# ይብላኝ ለወይኒቱ!



አይሆንም እያለች ልሳምሽ ቢሏት፣
አይሆንም እያለች እናግባሽ ቢሏት፣
ስንቱን ሽማግሌ አማጭ ላኩባት፣
መምህሩም በመስቀል ቢያወርዱ ግዝት፣
ቀልድ መሰሎ ታያት እንደ ልጅ ተረት…

ወይ ገዳም ግቢና መንኩሺ በወግ፣
ወይም እንዳርሽ፣ እንድንበላ ሰርግ
ጊዜው ሳያልፍብሽ የትዳር መዓርግ
ወልደሽና ከብደሽ በትዳር፣ በሕግ!
ካልሆነ'ማ አፈር ነሽ፣ ነገ ወደ ፍግ…

ጥፍሯንም በቀለም አሽቀረቀረችው፣
ከንፈሯን በቀለም አሽቀረቀረችው፣
በዕሾኽ፣ በሽቦ ራሷን ያጠረችው፣
መልኳና ውበቷን እንዳፈቀረችው፣
ይብላኝ ለወይኒቱ፣ ቆማ ለቀረችው…

ገ/ኢ. ጐርፉ።

# ይብላኝ ለወይኒቱ ፪



ወይኒቱ! ወይኒቱ! ተሽቀርቃሪቱ!
ሊያንቅሽ ብሎ ነበር ትዕቢቱ፣ ኩራቱ
ስትሽቀረቀሪ አለፈ ሰዓቱ
መልክሽ፣ ውበትሽም ረገፈ በከንቱ

ሲያምር የነበረ ውበት፣ ቁንጅናሺ
ያየሽም ሰው ሁሉ እንዲያ ሲመኝሽ
ማንም አይነካኝም ስትዪ ኮርተሽ
ዘመንሽ አለፈ፣ ከንቱ ጠወለግሽ!
በጣም ያሳዝናል መጨማደድሽ፣
በጣም ያሳዝናል መሸማቀቅሽ!
ሲያምር የነበረ ዕፁብ ውበትሽ
ዛሬ ምን ትሆኚ፣ ምንስ ይዋጥሽ?

የተሽሞነሞንሽው፣ የተሽቀረቀርሽው
ይብላኝልሽ ላንቺ ቆመሽ ለቀረሽው!



ገ/ኢ. ጐርፉ።

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot**. You may contact G.E. Gorfu for comments at** gegorfu@yahoo.com**.***